**ቅዱስ ሲኖዶስ**
The Holy Synod
4127 Redwood
Oakland, CA 94610
(510) 530-3681



# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክ/ቅ/ሲኖዶስ

## ፩ - ቅዱስ ሲኖዶስ

ብሂል (ትርጉም) ሲኖዶስ ማለት ቃሉ የጽርዕ (የግሪክ) ሆኖ ትርጉሙ ዐቢይ ጉባዔ ጳጳሳት ወይም የቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ጉባዔ ማለት ነዉ። (Synod's Ecclesiastical Assembly)

በእጥቢያዉ፣ በአዉራጃዉና፣ በየክፍለ ሕገሩ ስለሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ካህናት ዉይይት ያደርጋሉ፣ ስብሰባ ያካሂዳሉ፣ ሴሚናር ይሰማሉ፣ ልዩ ልዩ ማኅበር ያደራጃሉ ግን የዚህ ሁሉ ዉጤት ቀርቦ ቋሚ ዉሳኔ የሚያገኘዉ፣ እዉነቱና ትክክለኛነቱ የሚለካዉ፣ ሕግ የሚያወጣለት ሕግን የሚተረጉምለት በበለጠም ሕግን የሚፈፀምበት የቤተ ክርስቲያን ጉባዔ ሲኖዶስ የሚባለዉ ነዉ። ይህም ስም ከ፪ ቃላት ተጋጥሞ የወጣ ነዉ። ሲን ማለት ጋር ወይንም ጋራ ማለት ነዉ ኦዶስ ማለት ጎዳና ማለት ነዉ። ተጫፍሮ ሲነበብ ሲኖዶስ ተብሎ ሲነገር የጋራ ጉዞ የጋራ ስምምነት ስለሚሆን በእዉነትና በትክክል የሚፈፀሙት ቤተ ክርስቲያን ነክ የሆኑ ዉሳኔዎች ስለሆኑ ሲኖዶስ ተብሏል፤ በተለይም ሲዉል የሚገባዉ ለቤተ ክርስቲያን ጉባዔ በተለይም ለጳጳሳት ጉባዔ ነዉ።

እንግዲህ ሲኖዶስ ስንል አንዲት ራሷን በራሷ የምታስተዳድር ከማንም ተፅዕኖ የሌላት ቤተ ክርስቲያን ጳጳሳት ብዙዎችም ጥቂቶችም ቢሆኑ ሕግ አዉጥተዉ ሥርዓት ይዘዉ የሚያደርጉት ጉባዔ ሲኖዶስ ነዉ፣ ሲኖዶስም ይባላል።

ሲኖዶስ በበለጠ ቃሉ የሚታወቀዉ ተፈፃሚነትም ያለዉ በምስራቅ ቤተ ክርስቲያን ነዉ። በምዕራቡ ዓለም በቃሉ ብዙ አይጠቀሙበትም አፈፃፀሙም ከምስራቁ ዓለም በጣም የተለየ ነዉ።

በምስራቁ ዓለም ግን ቤተ ክርስቲያን ተብሎ ከተቋቋመ ሲኖዶስ የሌለዉና በሲኖዶስ የማይመራ ቤተ ክርስቲያን የለም ሊኖርም አይችልም።

በምዕራቡ ዓለም ግን በተለይም በፕሮቴስታንቱ ዘንድ በቀላሉ ቤተ ክርስቲያን እንደከልት አድርገዉ በየጊዜዉ በየቦታዉ ማቋቋም ስለሚቻል አንድ ሰዉ እርሱ በመሰለዉ ይመራዋል ያስተዳድረዋል እንጂ ሐዋርያዊ ትዉፊት ስለሌለዉ፣ በሐዋርያዊ ትዉፊትም ስለማይመራ ሲኖዶስ የሚለዉ ቃሉን ተግባሩንም አይጠቀሙበትም። አንዳንዶች የኛም ወገኖች ይኸን የመሰለዉን ሥርዓት አልበኝነትን ተከትለዉ ቤተ ክርስቲያን እያሉ በግላቸዉ ያቋቁማሉ።

የኛ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ከምስራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያን ዉስጥ አንዷ ስለሆነች የምትመራዉ በሐዋርያዊ ትዉፊት ስለሆነ በቅዱስ ሲኖዶሳዊ ዉሳኔ ታምናለች ቅዱስ ሲኖዶስንም ትቀበላለች፤ እርሱ በሚሰጣት መመሪያ ትመራለች።

በአሁኑ ጊዜ በቤተ ክርስቲያናችን ላይ ከባድ ችግር ስለደረሰባት ቤተ ክርስቲያኗ በዓለም ተበትና በስደትና በመከራ ትገኛለች። ይኸን የተበተነ ሕዝብ ለማሰባሰብ ደግሞም ቤተ ክርስትያኗን በአንድነቷ ጸንታ እንድትኖር ከቤተ ክርስቲያኗ ጋር የተሰደደዉ ሲኖዶስ ቀኖናዊነቱን አስመስክሮ ሕጋዊነቱን አጽድቆ ቤተ ክርስቲያኗን በመምራት ላይ ይገኛል፤ ከዚህም አፈንግጠዉም እንደከልት የሚመሩ አሉ! ለስደተኛዋ ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ያለ ዕድል ስታገኝ [illegible]፣ ሥርዓቷን የሚጠብቅ ተቋም ስታገኝ በደስታ በመቀበል ፋንታ ተቃራኒ ሆኖ መቅረብ የሚያሳዝን ነዉ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በብዛት በሰሜን አሜሪካ፣ በካናዳና በአዉሮፓ በአዉስትራሊያ፣ በአፍሪካ ተበትና የምትኖር ስትሆን በአሁኑ ጊዜ ፈጥኖ የሚደርስላት፣ የተቻለዉንም ያህል ርዳታ የሚሰጣት ይኸዉ በስደት ያለዉ ቅዱስ ሲኖዶስ ነዉ፣ ሕዝቡም ተስፋ አድርጎ የሚጠባበቀዉ እርሱን ነዉ።

ለስደተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን ደጋፊዋ ይኸዉ የስደት ሲኖዶስ ነዉ። በስደትም የምትገኘዉ ቤተ ክርስቲያን ሁሉ በስደተኛዉ ቅዱስ ሲኖዶስ ሥር መተዳደር ግድ አለባት፤ ይኽ እዉነት ነዉ። ከሀገር ቤት ተሰደድኩኝ ብሎ መጥቶ በስደት ሀገር ቤተ ክርስቲያን በግሉ አቋቁሞ እኔ የአዲስ አበባዉን ሲኖዶስ ነዉ የምቀበለዉ ማለት ወይም ከሁለቱም ጋር አይደለሁም የእኔ ቤተ ክርስቲያን ነፃ ናት የሚለዉ  አስተያየት ትርጉም የለሽ አነጋገርና የማይገባ እንቅቅልሽ ነዉ፣ ወይም እንደፈለገኝ ብሆን This is America ማለት ነዉ።

የአዲስ አበባዉን ሲኖዶስ መቀበሉም መልካም ነዉ ግን እርሱን ከተቀበለ መጀመሪያ ምን አሰደደዉ ወይም የአዲስ አበባዉን ሲኖዶስ የሚቀበል ከሆነ የአባ ጳዉሎስን ስም የማይጠራ የአዲስ አበባዉን ሲኖዶስ ዉሳኔዉንም የማይቀበል ለምንድን ነዉ ? በቤተ ክርስቲያን ላይ ሽፍጥ ተገቢ ነዉን ? የሚያዉቅብኝ የለም ነዉን ! በመሰረቱ ቤተ ክርስቲያን ለምንና ለምን ተከፈለች? ቤተ ክርስቲያን ለምንስ ተሰደደች? እነዚህ ሁለት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ማግኘት አለባቸዉ። እዉነተኛ ክርስቲያን በእዉነት ከተናገረ መልሳቸዉ ቀላል ነዉ ነገሩ ግልጥ ነዉ የማይታወቅ እያስመሰሉ የሚናገሩ ቢኖሩም እንደሚከተለዉ ይገለጣሉ።

ሀ - የቤተ ክርስቲያን ስደት በሀገር ቤት ያለዉ ሲኖዶስ ሕገ ወጥ በመሆኑ፣ በሕገ ወጥ ፓትርያርክም በመመራቱ፣ ሕገ ወጥ ዉሳኔዎችም በየጊዜዉ በመተላለፋቸዉ ከእነዚህ ሕገ ወጥ ሰዎች አልተባበርም ከማህበራቸዉም አልሳተፍም በሕገ ወጥነት ከሚሰሩ ተግባሮችም አልተባበርም በማለት ስደቱን ተያይዞታል የስደቱም መነሻ ይኸ ነዉ።

ታዲያ ራሱ ከዚያ ባለ ሲኖዶሱን ጠልቶ ከወጣ በኋላ የዚያን ሲኖዶስ ነው የምቀበል፣ የዚያን ሲኖዶስ ነው የምደግፍ የሚለዉ ከምን የተነሳ አነጋገር ነው ትክክለኛ አነጋገር ነዉን ? ወይስ ከስህተት ወደስህተት እየተራመዱ ሌላዉን ማሳሳት እንደ ቅዱስ ተግባር ተቆጥሮ ነው ?

ለ - ቤተ ክርስቲያኗ ደግሞ የተከፈለችዉ ጎሳን ቋንቋን ተከትሎ እዉነቱን ዘንግቶ ከመራመድ የተነሳ የተፈጠረ ከፍተኛ ስህተት ነዉ እንጂ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አትከፈልም ነበር። በመሰረቱ ቤተ ክርስቲያን ዓለም አቀፋዊ መንፈስ ያላት (ዩንቨርሳል) እንጂ በወንዝ በቋንቋ፣ በጎሳ የምትከፋፈል አልነበረችም። እንዲያዉም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እስከ ቅርብ ጊዜ በግብፃዊ ጳጳስ ስትመራ የነበረች፣ ቋንቋዉን በማታዉቀዉ ጳጳስ ስትመራ፣ ቋንቋዋን የማያዉቅ ጳጳስ ሲመራት ነበረች። ግን አሁን የእገሌ አገር ጳጳስ፣  የእገሌ አገር ፓትርያርክ አይመራንም፣ አያስተዳድረንም በማለት የዘርና የወንዝ ልዩነት በተጠናወታቸዉ ሰዎች ምክንያት ቤተ ክርስቲያን ልትከፈል ችላለች። ለዚህ ትልቅ ጥፋት ካህናት ነን የሚሉ በመጠኑ ይገኙ እንጂ ትልቁን የመከፋፈል መርሆ አንግበዉ ሁሉን የሚያስቱ የፖለቲካ ሰዎች ናቸዉ። ቤተ ክርስቲያንን የነርሱ ማስከ አድርገዉ የነርሱን ደባ ለማካሄድ ይፈልጋሉ። የሚያስከትለዉ ጥፋት ከፍተኛ መሆኑን እነርሱም በቀላሉ ይመስከቱታል ካህናቱም ሆኑ የፖለቲካዉ ሰዎች የመለያየቱን ጥፋት እነርሱ አጥፍተዉ በሌላዉ ለመለከክ ይፈልጋሉ። የዘርን የጎሳን ልዩነት ወደኋላ በመተዉ ሁሉም ቤተ ክርስቲያኖች አንድ እንዲሆኑ ቢደረግ መልካም ነበር። ክርስቲያኖች ካልተባበሩ ዘረኛን አወቅንብህ ተወን ብለዉ አዉግዘዉ ወደ እዉነተኛዉ ሕጋዊ ክርስቲያናዊ አመራር ካልገቡ ይህች የተሰያየች ቤተ ክርስቲያን ትወድቃለች ፈጽማም ትጠፋለች። በዚያን ጊዜ ሕዝቡም ታሪክ የለሽ፣ ሐይማኖትም የለሽ ሆኖ ይቀራል።

## ፪ - የሲኖዶሱ ቦታ

ለአንዲት ቤተ ክርስቲያን አመራር ቅዱስ ሲኖዶስ ያስፈልጋል፣ ቅዱስ ሲኖዶስም መኖር አለበት ብለናል፣ ታዲያ የዚያች ቤተ ክርስቲያን መሪ የሲኖዶሱን ስብሳቢ የሆነዉ ፓትርያርክ፣ ሊቀ ጳጳስ ሲኖዶስም የት መሆን፣ የትስ መኖር አለበት መልሱ አጭር ነዉ። ፓትርያርኩ ወይም ሊቀ ጳጳሱ እርሱ በተገኘበት፣ እርሱ በሚኖርበት ወይም እርሱ በፈቀደበት ቦታ ይሆናል። ለምሳሌ ፫ቱ ዐበይት ሲኖዶስ የሆኑት የመጀመሪያዉ በኒቅያ፣ ሁለተኛይቱ በቁስጥንጥንያ፣ ሦስተኛዋ በኤፌሶን ነዉ የተደረገዉ

፫ቱም በዛሬዉ ቱርክ ግዛት ነዉ። የዚያን ጊዜ ሊቀ ጳጳስ የነበረዉ የሮሙ ሲሆን እርሱ ባለበት በሮም አልተደረገም ነገር ግን በተፈቀደበት ቦታ ሆኗል። እንዲሁም አህጉራዊ ሲኖዶስ በየቦታዉ ሲደግ ይኖር ነበር ለምሳሌ ጋንግራ፣ አንክራ፣ አንጾኪያ . . . ሌሎችም ብዙዎች በየቦታዉ የተደረጉ አሉ። ይኸንም ለመረዳት ሲኖዶስ የተባለዉን መጽሐፍ ማንበብ በቂ ይሆናል።

የኢትዮጵያም ሲኖዶስ ለዐሥራ መቶ ዓመትና ከዚያም በላይ ሲደረግ የኖረዉ ቀድሞ አሌክሳንድርያ፣ በኋላም ካይሮ ነዉ ምክንያቱም ፓትርያርካችን ይኖር የነበረ በዚያ ነዉና። በኋላ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ራሷን ችላ ሊቀ ጳጳስ፣ ፓትርያርክ ሲኖራት ቅዱስ ሲኖዶስ በአዲስ አበባ መደረግ ተጀመረ።

አሁን ደግሞ ሕጋዊዉ ፓትርያርክ ቤተ ክርስቲያኗም አሜሪካ ስለሚገኙ ቅዱስ ሲኖዶስ በአሜሪካ በካናዳ ሊሆን ይችላል፣ የሚከለክልም ሕግ የለም።

አዉነተኞች ክርስቲያኖች ቢኖሩ ኖሮ ፓትርያርካችን ለምን፣ እንዴት ይሰደዳሉ በማለት ሊጮሁ፣ ድምፅም ሊያሰሙ ኀዘናቸዉንም ሊገልጡ ይገባቸዉ ነበር። ከሲኖዶሱ ይልቅ የቅዱስነታቸዉ ሕይወት ይበልጥ ነበርና። በመንበራቸዉ መገኘት ተገቢ ነበር ለፓትርያርኩ ክብር፣ ሕይወት ሳይታሰብ ሲኖዶሱ የት መሆን አለበት ማለት ምኝነት ነዉ።

መጮክ የሚያዳግታቸዉ የሚያስቸግራቸዉ ነገር ቢኖር ደግሞ ክርስቲያን የሆነዉ ሕዝብ ሁሉ ተባብሮ የፓትርያርኩ ሕይወት የሚጠበቅበትን፣ የቤተ ክርስቲያናችን ክብርና ቅድስና አንድነቷም የሚጠበቅበትን ሥራ በኅብረት መስራት አስተያየትም ማዉጣጣት ይገባዉ ነበር። ግን አፍሪካዊ ስሜት በርትቶ፣ ኅብረት ጠፍቶ ሁሉም በአልሆነ መስመር ገብቶ ይዳክራል።

አሁንም የሲኖዶሱ ቦታ አዲስ አበባ ነዉ እያሉ ከማስተጋባት ይልቅ ፓትርያርኩ መሰደድ የለባቸዉም ወደ ሀገራቸዉ ይመለሱ እያለ ክርስቲያኑ ሁሉ መጮህ በገንዘብም መርዳት፣ በሐሳብና በጉልበት በሌላም በሚያስፈልገዉ ነገር ሁሉ መርዳት ተገቢ ነበር። ይሁን እንጂ የጎላዉ ልዩነት አይኑን አሳዉሮት ለሁሉም ይኸ ሁሉ ሊታየዉ አልቻለም፤ በዚህም ፈንታ ለምን ተሰደዱ ለምን ከዚያ አልሞቱም ከዚያ ቢሞቱ የኛ ወገን ይሾም ነበር በማለት የጥላቻ መልዕክታቸዉን ያስተላልፋሉ ድምፃቸዉን ያሰማሉ። የብዙዎቹ አስተያየት ፓትርያርኩ በገዴትና በብስጭት ይሙቱ ቤተ ክርስቲያኗም በመከፋፈል ትድከም ሕዝቡም አንድነት አጥቶ ተበታትኖ ይኑር የሚል ቁርጥ ዉሳኔ የወሰዱ ይመስላል ምክንያቱም እየዋሉ እያደሩ በማፈር ፈንታ ይህንኑ በማፅናት አዲስ ሰዉ ሲመጣ እርሱን እቅፎና ደግፎ የጥፋቱ ተባባሪ እንዲሆን በመያዝ ሳልሰሙት በግልፅ ያለሐፍረት በማስማት ቤተ ክርስቲያኗን ለማፍረስ የህዝብን አንድነት ለመለያየት ተግተዉ በግልጥ ሲሰሩ ይታያሉና።

በእንዃሩ ግን ይኸ እኛ የምናካሂደዉ ሲኖዶስ ቅዱስ ነዉ፤ ሕጋዊም ነዉ። ምክንያቱም ፓትርያርኩ ሕጋዊ ፬ተኛ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ናቸዉና። የቅዱስ ሲኖዶሱ አባላትም በህግ የተሾሙ ሊቃነ ጳጳሳት ናቸዉ እንዲያዉም በመጨረሻ ጊዜ በቋሚ ሲኖዶስ ዓባልነት ተመርጠዉ እንዲሰሩ ተወስኖ የነበሩ ናቸዉ።

ቅዱስ ሲኖዶስም ጥንታዊ መልኩን ጥንታዊነቱን እንደያዘ ሕጋዊ አሰራር እንዲኖረዉ በአሜሪካ መንግስት ተመዝግቦ ሕጋዊ ቦታዉን ይዞ በመስራት ላይ የሚገኝ ነዉ። ዋና አላማዉም ቤተ ክርስቲያንን አገናኝቶ አንድነቱን አፅንቶ ለመምራት ነዉ። የጎማዉ ጨለማ ዓይኑን ካልሰወረዉ በቀር ይህ ግልጥ የሆነ ለሁሉም የሚረዳ ዓላማ ነዉ። ለቤተ ክርስቲያን አመራር ከዚህ የተሻለ ዘዴና መልክ ሲኖር አይችልም ደግሞም አይኖርም። ከጥንቱ ጀምሮ ቤተ ክርስቲያን የምትመራዉ፤ የምትተዳደረዉ በቅዱስ ሲኖዶስ ዉሳኔ መሰረት ነዉና።

ቤተ ክርስቲያኗ ትጥፋ ሕዝቧም ይለያይ ይበተን የተባለ እንደሆን አሁን የተያዘዉን የጥፋት ጎዳና መከተል ነዉ። ያለዚያ እራሱ ተሰዶ በስደት አገርም ቤተ ክርስቲያን አቋቁሞ የአዲስ አበባዉን ሲኖዶስ ነዉ የምቀበለዉ የሚለዉ አነጋገር ቅሬትም ይሆናል ነዉ። ወይም ከአሁን ጀምሮ የአባ ጳዉሎስን ስም መጥራት፣ በእርሳቸዉ የሚመራዉን ሲኖዶስ ዉሳኔ መቀበልና መስራት።

አሁን በስደት ላይ ያለዉን የሲኖዶስ አመራር አንቀበልም ጳጳስ የሚሉትን አንቀበልም በዓይናችንም ልናይ አንፈልግም

የሚል አንነጋገር አለ ስጊዜዉ አሁን ሌላ አዛዥ ናዛዥ እንዳይኖር፣ እንደ ሐሳባችን እንሰራለን፣ እንደፈቀድን እንመራለን በማለት ነዉ። ከሀናቱም ሕዝቡም ይህንን አቋም ወስዷል፣ ግን ወደፊት ቤተ ክርስቲያን የምትባል አትኖርም የህዝብም አንድነት አይገኝም። አባቶች ሲመስሉ "የዉዉ ገደል ሲናድ ብልህ ያለቅሳል ሞኝ ግን ይስቃል" ይላሉ፤ ብልሆች በዚህ በአሁኑ ይዘት በቅዱስ ሲኖዶስ ቤተ ክርስቲያን ካልተመራች ትጠፋለች ብለዉ የሚያለቅሱ የሚያዝኑም ብዙዎች ናቸዉ፣ ሞኞች ግን ቤተ ክርስቲያን ከሲኖዶስ ዉጭ ሆና ወደ ጥፋት ስትጓዝ ይስቃሉ መለያየቱንም ያስፋፋሉ አንድነቱን ያጠፋሉ።

ከላይ እንደተረዳነዉ የሲኖዶሱ ቦታ ፓትርያርኩ ባሉበትና እርሳቸዉ በባረኩትና በፈቀዱት ቦታ ይሆናል፤ ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን የሆነ ሁሉ የሲኖዶስ አባል በመሆን ቤተ ክርስቲያን በአንድነት እንድትመራ ቢደረግ መልካም ነዉ ይህም ዕድል ባያመልጥ!

## ፫ - ቅዱስ ሲኖዶስ መቼና ወዴት መደረግ አለበት፤

ቅዱስ ሲኖዶስ በአመት ሁለት ጊዜ እንዲደረግ የቤተ ክርስቲያናት ሕግ ፍትሐ ነገስቱ እንዲህ ሲል ይናገራል "ሁለተኛ ኒቅ ፭። ኒቅ፤ ፵፭። በየቦታዉ ሁሉ ኤጲስ ቆጶሳት በየዓመቱ ሁለት ጊዜ ከጳጳሳቸዉ ወይም ከሊቀ ጳጳሳቸዉ ዘንድ ይሰብሰቡ። መጀመሪያ ከፆመ አርባ በፊት ይሁን፤ ከፉንና ቁጣን በሚያርቁ ገንዘብ፣ ቁርባናቸዉ ለእግዚአብሔር ንፅህት ከብርት ቅድስት ትሆን ዘንድ ሁለተኛዋም ከበዓለ መስቀል በኋላ በመከር ወራት ይሁን። በበጋና በበልግ ወራት ቸነፈር የድንገት ሞት ይበዛልና ከሞት አስቀድሞ ፍቅር ሰላም ይሆን ዘንድ። ወደ ጌታችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ በፍፁም ንፅሆና በሚቀርቡ ገንዘብ። ከካህናት ወገን ወይም ከህዝቡ ወገን ሁና ኤጲስ ቆጶሱ አዉግዞ የለየዉን ሰዉ ፍርድ ይመረምሩ ዘንድ፣ ወይም ይህን በሚመስል ነገር ሁሉ እንደተገለፀላዉ ይፈርዱ ዘንድ" (ፍትሀ ነገ አንቀፅ ፭ ቁጥር ፩፻፷፭)።

በዚህ መልክ ከብዙ ቦታ ላይ ተጠቅሶ ተንግሮ እናገኛለን፣ ይሁን እንጂ በዓመት ሁለት ጊዜ በመሆን ፈንታ አስቸኳይ ጉዳይ ሲገኝ ፓትርያርኩ በወሰነዉ ጥሪውን ባስተላለፈበት ጊዜ መላልሶ ሲኖዶስ ሲደረግ ይቻላል።

የቤተ ክርስቲያን አንድነት የሚገኘዉ፣ የስነ ስርአቱ የጸሎቱ፣ የትምህርቱ ሁሉ አንድነቱ የሚጠበቀዉ በቅዱስ ሲኖዶስ ዉሳኔ ነዉ። ቅዱስ ሲኖዶስ የቤተ ክርስቲያኑ ራስ ስለሆነ ጤነኛ ራስ ካለ ዘንድ አካሉ ሁሉ ጤነኛ እንደሚሆን ጤነኛ ቅዱስ ሲኖዶስ ካለ ዘንድ ጤነኛ ወይም እዉነተኛ ቤተ ክርስቲያን ትኖራለች (ትገኛለች)። ከቅዱስ ሲኖዶስ ዉጭ እየተራመዱ ቤተ ክርስቲያን ነን፣ ካህናት ነን የሚሉ ሁሉ ምንደኞች ናቸዉ (ዮሐ. ፲:፲፪)። ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን አይጠብቁም፣ ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያንም በስርአተ ቤተ ክርስቲያን መሰረት አይፈጽሙም። ቅዱስ ሲኖዶስ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እንግዳ ሥርዓት፣ አዲስም ሥርዓት ሳይሆን ሐዋርያዊ ትዉፊት እንደመሆኑ የቆየ የታወቀ ነዉ። ቅዱሳን ሐዋርያት የቤተ ክርስቲያንን ችግር በሲኖዶስ አማካይነት ባያስወግዱ ኑሮ አያንዳንዳቸዉ እንደፈለጉ ዉሳኔ ቢያስተላልፉ፤ ፩ኛ- ዉሳኔዉ የወል አይሆንም ተቀባይነትም አይኖረዉም ነበር። ፪ኛ- ለዛሬዉ አመራራችን መነሻ የሚሆነን አይገኝም ነበር። አሁን ግን የሐዋርያትን ፈለግ በመከተል በቅዱስ ሲኖዶስ ዉሳኔ መሰረት ቤተ ክርስቲያን ትመራለች ትራመዳለች ስራዋንም እያከናወነች ትገኛለች። (የሐ.ሥራ ፲፭.፮-፳፱)

ብዙዎች ከልት የሆኑ ወይም የልዩ ልዩ የፕሮቴስታንት ቅርንጫፎች የሆኑ የተለያዩ ድርጅቶች ስመን ቤተ ክርስቲያን ግብሩን የንግድ ድርጅት አድርገዉ የሚያካሂዱና የሚሰሩ በዘመናችን ይገኛሉ። እንዲሁም በኛ ቤተ ክርስቲያን ስም የሚነግዱ ሊቀ ጳጳስ፣ ጳጳስ አያስፈልግም፣ ሲኖዶስም አንቀበልም በማለት የሚያስተምሩ የሚሰሩ ይገኛሉ፣ ምዕመናን ግን ዉስጣዊ ተንኮላቸዉን እያዉቁም ቤተ ክርስቲያን የሚለዉን መርሆ ብቻ ያስባሉ እንደነዚህ ካሉት አስመሳዮች መጠንቀቅ የአዋቂዎች ፋንታ ነዉ።

## ፬ - የቅዱስ ሲኖዶስ አስፈላጊነት

ቅዱስ ሲኖዶስ ከተለያዩ ሀገረ ስብከት የተዉጣጡ፣ የተለያዩ የቅድስና ሕይወት ያላቸዉ፣ የተለያዩ ዕውቀትና [illegible]

ያሳቸዉ አባቶች ጳጳሳት በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ተሰብስበዉ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ፣ እንደ አንድ ልብ መካሪ ሆነዉ፣ ራሳቸዉን በእዉነት አስገዝተዉ የሚወያዩት፣ የሚወስኑት ዉሳኔ ለቤተ ክርስቲያንና ለክርስቲያናዊ ኅብረተሰብ መድኃኒት ነዉ፣ የአንድነትም ዓርማ ነዉ፣ ስለዚህ ለቤተ ክርስቲያን በጣም አስፈላጊ ነዉ።

ጌታ በዐረገ በ፶ኛዉ ዓመት በአዲስ አማኞችና በሐዋርያት ዘንድ ተነስቶ የነበረዉን አለመግባባትና ክርክር ሐዋርያት የፈቱት በሲኖዶስ ነዉ (የሐዋ ፲፭.፮-፳፱) ያን ጊዜ እንጳዉሎስ ለብቻቸዉ እንደመሰላቸዉ ወስነዉ አስተላልፈዉ ቢሆን፣ እንጴጥሮስም በበኩላቸዉ በግላቸዉ ዉሳኔ አስተላልፈዉ ቢሆን ኑሮ፣ የኢየሩሳሌም ኤጲስ ቆጶስ ያዕቆብም የግሉን ዉሳኔ አስተላልፎ ቢሆን ፩ኛ በዚያን ጊዜ የነበረዉ ክርክር አይበርድም፣ ፪ኛ ለዛሬም ለኛ መመሪያ መነሻም የሚሆን ምክንያት አይኖረንም ነበር፣ ነገር ግን በዚያን ጊዜ ቅዱሳን ሐዋርያት በመንፈስ ቅዱስ ተመርተዉ በሲኖዶስ ችግራቸዉን አስወግዱ ለዚያች ቤተ ክርስቲያን ሰላም አስገኙላት። ዛሬም ለምንገኝ ለኛ ትልቅ ምሳሌነታቸዉን አስተላለፉልን።

በዚህ ሁሉ ምክንያት የቅዱስ ሲኖዶስ አስፈላጊነት ከፍተኛ ነዉ። በዘር፣ በቀለም፣ በቋንቋ በጂዖግራፊ የተለያየ ሕዝብ የሚገኝባት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን አንድነት ተጠብቆ እንዲኖር ያደረገዉ በቅዱስ ሲኖዶስ ዉሳኔ መሠረት በመሥራት ነዉ። እንሆ ዛሬ "ነፃ" ቤተ ክርስቲያን (inependent Church) እያሉ በየጎጡ ከፋፍለዋት የሚገኙ ምንደኞች ሲኖዶስን አንቀበልም የሚሉት በሥነ ሥርዓት ላለመሔድ፣ ሕገ ቤተ ክርስቲያንን ለማፍረስ፣ በምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን ለመጫወት የቤተ ክርስቲያንን አንድነት ምሽግ ለመናድ ነዉ። ሕዝብ ደግሞ እነርሱንም ካህናት ብሎ ወይም አድርጎ እንደከልት አድርገዉ ያቋቋሙትን ድርጅት እንደቤተ ክርስቲያን እየመሰለዉ፣ ወይም እያደረገ በመገኘቱ ቁጥሩ እየበዛ ሲሄድ ይገኛል። ሕገ ወጡም እየበዛ ሥርዓት አልበኝነት በግልጥ እየታየ ይገኛል። ግን ሰይጣን አሸክላዉን በሰሬዉ የዘረጋበት ጊዜ በመሆኑ በዚህ ወጥመድ እየተያዙ በከልት እስር ቤት የታጎሩ ብዙዎች በመሆናቸዉ እንደነቅም ምክንያቱም በዘመኑ መጨረሻ ብዙ ሕገ ወጥ ሥራ በክርስቲያኖች መካከል እንደሚሰራ መጻሕፍት አስቀድመዉ ተናግረዋልና። (፩.ጢሞ. ፬.፩-፫ ፤ ፪ጢሞ. ፫.፩-፱) ለማማታት ቢሉ ሲኖዶሱ ያለ አዲስ አበባ ነዉ ይላሉ፣ ግን የአዲስ አበባዉን ሲኖዶስ ዉሳኔ አንድ ቀንም እንኳ ተቀብለዉ ተግባራዊ አድርገዉት አያዉቁም ምነዉ ወይስ ለምንድን ነዉ ሲሏቸዉ ስደተኞች ነን ቤተ ክርስቲያንም በስደት አገር ነዉ ያለችዉ የአዲስ አበባዉ ቤተ ክርስቲያን አመራር ትክክል አይደለም ይላሉ፤ ይህም የሊሊት ወፍ የተባለችዉ አይጥ ሲሏት ክንፏን ታሳያለች ወፍ ሲሏት ጥርሷን ታሳያለች እንደሚባለዉ ነዉ። ለምንድን ነዉ በስደተኛዉ ሲኖዶስ የማትመሩት ሲሏቸዉ የስደተኛዉን ሲኖዶስ የማንቀበለዉ እኛ የአዲስ አበባዉን ስለምንቀበል ነዉ ሲኖዶስም ያለዉ አዲስ አበባ ነዉ ዉጭ አይወጣም ይላሉ ግን ትክክለኛ መልስ አይደለም፤ ሲኖዶሱ ቀድሞ የነበረዉ ካይሮ ነበር በኋላም አዲስ አበባ ሆኗል ዛሬ ደግሞ አሜሪካና ካናዳ የማይሆንበት ምክንያት ሊኖር አይችልም፤ ምክንያቱም ፓትርያርኩ ያሉ በስደት አገር ነዉና። እንግዲህ ይህንን ሁሉ ያተትነዉ ለማወቅ ለሚፈልጉ ብቻ ነዉ ቅዱስ ሲኖዶስ የቤተ ክርስቲያን ችግር መፍቻ ብቸኛ ማዕከል ነዉ፤ የቅዱስ ሲኖዶስ አስፈላጊነትም ለእዉነተኛና ትክክለኛ ቤተ ክርስቲያን አመራርር የአንድነት አጠባበቅ የምስጢራትን አገልግሎት በትክክል እንዲሰጥ የሚያደርግ ነዉ። የቤተ ክርስቲያን የአንድነቷ ምልክት ቅዱስ ሲኖዶስ ከሆነ ቤተ ክርስቲያንም በአንድነት ለመሄድ ቅዱስ ሲኖዶስን መቀበል ግዴታ ነዉ።

ቅዱስ ሲኖዶስ ካለ ዘንድም ማንም እንደፈለገ በራሱ ፈቃድ ቤተ ክርስቲያንን አይከፍትም በራሱም ፈቃድ ቤተ ክርስቲያንን ሊመራ የሚችል የለም። ቅዱስ ሲኖዶስ ካለ ዘንድ ማንኛዉም ቤተ ክርስቲያን አንዱ ከሌላዉ ተለይቶ አይሰራም ልዩነቱንም አያሳይም። ከቅዱስ ሲኖዶስ ዉጭ የሆነ ከቤተ ክርስቲያንነትም ዉጭ ይሆናል፣ እንግዲያስ ቤተ ክርስቲያን የሚባለዉም ከመስጊዱም ከቴምፕሉም ከከልት ድርጅትም የሚለየዉ የለዉም።

## ፫ - የቅዱስ ሲኖዶስ ሊቀመንበር

የቅዱስ ሲኖዶስ ሊቀመንበር ሁል ጊዜ ፓትርያርኩ ነዉ ወይም የሐገሯ ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛዉ መሪ ሊቀ ጳጳስ ወይም ኤጲስ ቆጳስ ነዉ እንግዲህ ሆሮ አርኪዉ ፓትርያርክ ሊሆን ይችላል ወይም ሊቀ ጳጳስ ሊሆን ይችላል ከኤጲስ ቆጶሳቱ መካከል ከፍ ያለዉ የአስተዳደር ሥልጣን ሊኖረዉ ይችላል፣ ስለዚህ የሲኖዶሱ ሰብሳቢ ይሆናል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከፓትርያርክ ማዕረግ እስከትደርስ በሊቀ ጳጳስ ስትመራ ነበረች፤ በዚያን ጊዜ እንደኛዉ ሰብሳቢም ዉሳኔ ሲያስተላልፍ

ይችላል ሁኖም ይሆናል። እንዲሁም ከፍተኛዉ የቤተ ክርስቲያን መሪያችን ሊቀ ጳጳስ እንዲሆን የተወሰነበት ጊዜ ነበር፣ በዚያን ጊዜም የቅዱስ ሲኖዶስ ሰብሳቢ ሊቀ ጳጳሱ ሁኖ ብዙ ዉሳኔ አስተላልፏል ብዙ ሥራም ሰርቷል። እንደገናም የቤተ ክርስቲያናችን የመጨረሻዉ ቁንጮ መሪ ፓትርያርክ ሆኗል፤ እንግዲህ የቅዱስ ሲኖዶስ ሰብሳቢዉ ሊቀመንበሩም ፓትርያርኩ ነዉ። ይህም ከፍተኛ የቤተ ክርስቲያን ማዕረግ ሊገኝ የቻለዉ በታላቁና አርቆ በሚመለከተዉ ንጉሠ ነገሥት ቀ. ኃ. ሥ ልዩ ጥረት ነዉ።

ቤተ ክርስቲያናችን ለዚህ ማዕረግ መብቃቷ ወይም ይህንን ትልቅ ማዕረግ ለማግኘት ምንም ያሳየችዉ ትግል የላትም ዕዉቀቱም ስልቱም አልነበራትምና ተገቢነቱንም አታዉቀዉም ነበርና፤ ስለዚህ ነዉ ዛሬ እንዳገኙ የሚጫወቱበት ማለት በፓትርያርክ ላይ ፓትርያርክ በጳጳስ ላይ ጳጳስ መሾም ማዕረጉን ማዋረድ ቤተ ክርስቲያንንም መለያየት የቤተ ክርስቲያኗን አርምጃ ፈጽሞ ማስንካከል የሚደረገዉ። ፓትርያርክ ከሁሉ በላይ የሆነ የክርስቶስ እንደራሴ የቤተ ክርስቲያን ራስ የሲኖዶሱ ሊቀ መንበር የአበዉ ጳጳሳት አባት ነዉ። ፓትርያርክ የቤተ ክርስቲያናችን የመጨረሻዉ ማዕረግ የቤተ ክርስቲያናችን ርዕሰ የቅዱስ ሲኖዶስ ሊቀመንበር ስለሆነ ከክርስቶስ በታች ትልቅ ክብር የሚገባዉ ቅዱስ ቡራኬዉ የሚጠበቅ ቅዱስ ቃሉም የሚሰማ መሆን ነበረበት፣ ባለመታደል ግን ፓትርያርኩን እያንዳንዱ ክርስቲያን እንደግል ባላጋራ እየተመለከተ በተቃራኒነት በጠላት ዐይን እያየ ቤተ ክርስቲያንን ሲገነጥል ሲለያይም ቅዱሱን ሥርዓት ሲያፈርስ ቅር የማይለዉ ካህንና ክርስቲያን ሕዝብ ነኝ የሚል ይገኛል። የሌሎች አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ከቦታ ወደ ቦታ ሲዘዋወሩ የሚደረግላቸዉ የክብር አቀባበል የክብር መስተንግዶ ከፍ ባለ ፍቅር ይገለጣል። ይህም አድራጎት የወገኑን ታላቅነት የማይማኖቱን ጽናት በትክክል ያሳያል፣ ትንሽ ሁል ጊዜ ትንሽ ነዉ፤ ሌላዉንም አዋረድኩ እየመሰለዉ የእርሱን ታናሽነት ያንፀባርቃል፤ ይህም በዚህ ዐይን ሊታይ ይገባዋል።

በብዙ ቦታ የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ፓትርያርኩን አክብረዉ ሲቀበሏቸዉ ከፍ ያለም መስተንግዶ ሲያዘጋጁላቸዉ ሌላዉ በጎሳ በቋንቋ በሌላም ልዩ ልዩ የመለያየት መረብ የተተበተበ ስለሆነ የኢትዮጲያዊነትን መልክ ማሳየት አልፈለገም። ይሁን እንጂ ቤተ ክርስቲያናችን አሁንም የምትመራዉ በፓትርያርኩ ሰብሳቢነት በሚካሄደዉ ቅዱስ ሲኖዶስ ዉሳኔ መሠረት ነዉ። ፓትርያርኩ የቅዱስ ሲኖዶስ ሊቀመንበር ናቸዉ፤ በምድርም የእግዚአብሔር ወኪል ናቸዉ በመላ ኦርቶዶክሳዊያን ሕዝብ ዘንድ መከበር አለባቸዉ፤ ቃላቸዉ መሰማት ቡራኬያቸዉም መተላለፍ አለበት።

## ፮ - የቅዱስ ሲኖዶስ ዉሳኔ በሁሉ የጸና መሆኑ

ቅዱስ ሲኖዶስ በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመራና የሚሠራ እዉነት የሚነገርበት ጉባዔ በመሆኑ በእርሱ የተወሰኑትን ነገሮች ሁሉ በየቤተ ክርስቲያኑ መጠናት መጠበቅም ያለባቸዉ ግዴታዎች ናቸዉ። ማንኛዉም የቤተ ክርስቲያን ሕግ የሚጸናዉ፤ ዶክትሪኑ የሚጠበቀዉ፤ የቅዱስ መጽሐፍ ትርጉም ሳይፋለስ በትክክል የሚተላለፈዉ ትዉፊቱ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያኑ በትክክል ተጠብቆ እንዲሔድ ትምህርቱና ስብከቱ ይዘቱን ጠብቆ እንዲሔድ የሚያደርግ ቅዱስ ሲኖዶስ ነዉ። ከዚህ ቀደም ትርጉም ያላገኙ ቃላት መልስ ያልተሰጣቸዉ ጥያቄዎች ሁሉ ትክክለኛዉን ትርጉምና መልስ የሚሰጠዉ ቅዱስ ሲኖዶስ ነዉ፤ ዛሬም የሚፈጠሩ ችግሮች ቢኖሩ መፍትሔዉ የሚገኘዉ ከቅዱስ ሲኖዶስ ነዉ።

እንግዲህ በቅዱስ ሲኖዶስ ፈቃድ የተቋቋሙ አብያተ ክርስቲያናት ለቅዱስ ሲኖዶስ ዉሳኔ አፈጻጸም ተባባሪዎች ናቸዉ፤ ማንኛዉንም የቅዱስ ሲኖዶስ ዉሳኔ አክብረዉ ተቀብለዉ በሥራ የሚያዉሉ እንደ ዉሳኔዉም የሚሰሩ እነዚህ ናቸዉ መሆንም አለባቸዉ ከቅዱስ ሲኖዶስ ቁጥጥር ዉጭ ቤተ ክርስቲያን ነን እያሉ እራሳቸዉን የሚጠሩ ፩ኛ ካህናቱ ሕጋዊያን ካህናት ላይሆኑ ይችላሉ፤ መነኮሳቱም ትክክለኞች ላይሆኑ ይችላሉ ክህነትም ሳይኖራቸዉ ካህናት ነን እያሉ የሚናገሩ ይገኛሉ ስለዚህም ነዉ ጳጳሳት እንዲገቡብን አንፈቅድም ጳጳሳትም አያስፈልጉም በማለት ነዉራቸዉ እንዳይገለጽ ለብቻቸዉ የሚኀዙ።

ቤተ ክርስቲያን እየተባሉ እንደዚህ ያለ ወንጀል እየተፈጸመባቸዉ ሕዝቡም እያማ ጆሮ ዳባ ልበስ እያሉ የሚኀዙ ይገኛሉ ካህን ነኝ የሚለዉ ዋጋ ቢስ የሆነ አገልግሎት ሲሰጥ፤ ሕዝቡም አሜን ብሎ ሳይቀበል ሁለቱም በከንቱ ሲደክሙ ይገኛሉ ዐይን ልቦና ያለዉ ይህንን ሲመለከት በጣም ያዝናል። የቅዱስ ሲኖዶስ ዉሳኔ በየቤተ ክርስቲያኑ ቢጠበቅ መጀመሪያዉኑ ቤተ ክርስቲያን ሲመሰረት በጳጳሱ ቅዱስ ፈቃድ ይሆናል ለዚያም ቤተ ክርስቲያን በሞያዉ በንሕህናዉ በችሎታው ተስማሚ የሆነ ካህን ይመደብለታል። ያም ካህን ከእለት ወደ እለት ለቤተ ክርስቲያን ሕይወቱን ለመስጠት ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል፤

የሲኖዶሱን ዉሳኔ አክብሮ ይቀበላል ለምዕመናኑም ያስረዳል። ይህም ሁናቴ የነበረና አሁንም መሆን ያለበት ግዴታ ነዉ፤ በዚህ በአሜሪካ ቋሚ ሁኖ የተመዘገበ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ አለ፤ ይህም ቅዱስ ሲኖዶስ አዲስ ሳይሆን ከሐዋርያት ሲወርድ የመጣዉ የክርስቶስ እንደራሴ በሆነዉ ፓትርያርክና ሊቃነ ጳጳሳት ወደ አሜሪካ በብዛት ስለመጡ ያንኑ የቀደመዉን ሲኖዶስ ይዘዉ መጡ ማለት ነዉ፤ ይህም ከሆነ ቤተ ክርስቲያንዋን ምዕናን አክብረዉ መቀበል ነበረባቸዉ። በቤተ ክርስቲያንም መካከል መከፋፈል ስለሌለ ሁሉ በዚህ ቅዱስ ሲኖዶስ ሥር መተዳደርና ዉሳኔዉን አክብሮ መቀበል መያዝም መፈጸምም ግዴታ ይሆን ነበር። ለምሥራቅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሁሉ ዋናዉ መመሪያ የቅዱስ ሲኖዶስ ዉሳኔ ነዉ።

ጳጳሳቱ የሲኖዶስ አባላት እንደመሆናቸዉ ሁሉም ተስማምተዉ ተግባብተዉ የወሰኑት ነዉ፤ ካህናቱም በእነርሱ ቁጥጥር ሥር ስለሆኑ እንደራሳቸዉ ዉሳኔ አድርገዉ ይመለከቱታልና ተፈፃሚነት አለዉ። የእኛም ኦርቶዶክሳዊ ቤተ ክርስቲያን የምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት አባል ስለሆነች መመሪያዋ የቅዱስ ሲኖዶስ ዉሳኔ ነዉ።

## ፯ - ለአንዲት ቤተ ክርስቲያን ሲኖዶስ ማስፈለጉ

አንዲት ቤተ ክርስቲያን ስንል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አንዲት ናት። እንግዲህ ይህች እራሷን በራሷ የምታስተዳድር የራሷን ፓትርያርክ፣ ሊቃነ ጳጳሳት፣ ኤጲስ ቆጶሳት መርጣ የምትሾም ራሱን የቻለ መተዳደሪያ፣ ራሱን የቻለ ዓላማ፣ ራሱን የቻለ ስም ያላት ቤተ ክርስቲያን ናት።

ከሁሉ በፊት በሀገር ቤትም በዉጭ ሀገርም ብትገኝ የዚችዉ የአንዲቱ ቤተ ክርስቲያን ቅርንጫፍ እንጂ ከሌላ የተገኘች ስላይደለች የመጠሪያ ስሟ በዚያዉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተብሎ ነዉ። ይህም ልዩ ስም የቤተ ክርስቲያኗን ማንነት ገልጦ ያስረዳል ክርስቲያኑም ካህናቱም ይህን ስም በመጠበቅ ሲገኙ የቤተ ክርስቲያኗን ማንነት ይገልጣሉ። ከሌሎች ቤተ ክርስቲያኖች ጋር የምትገናኝበት ወይም የምትለይበት ራሱን የቻለ አላማ ዶክትሪን አላት። ይህም አላማ የቤተ ክርስቲያኗ አርማ ወይም ልዩ መታወቂያዋ ነዉ፤ ምን እንደምታስተምር በምን እንደምታምን ለይታ ወስና ትይዛለች የራሷ ምዕመናንና ካህናት እምነቷን በመጠበቅ በማስተማርና ለተተኪዉ ትዉልድ በማስተላለፍ የሚሰሩ በመሆናቸዉ ሌላዉ ቤተ ክርስቲያን ከርሷ ጋር በምን እንደሚገናኝና በምን እንደሚለያይ ተለይቶ ይታወቃል። የዚህች ቤተ ክርስቲያን ካህናት ዶክትሪኗን አላማዋን በአንድ ቃል የሚናገሩ የሚመሠክሩ ሁነዉ መገኘት አለባቸዉ። እራሳቸዉም አንድ ሁነዉ በአንድነታቸዉ የጸኑ ሆነዉ ሲገኙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አባል ስመሆናቸዉ መታወቂያቸዉ ይሆናል፤ ቤተ ክርስቲያኗም በዚህ ተግባራቸዉ ምን እንደሆነች ትታወቃለች በዚህም ትከበራለች። ካህናቱ ተለያይተዉ የተናገሩ የሰሩም እንደሆነ ወይም አንዱን አላማ በተለያየ ትርጉም የተረጎሙት እንደሆነ ቤተ ክርስቲያኗንም ከፋፍለዉ ያሳዩ እንደሆነ የእነርሱም ስም ይጠፋል የቤተ ክርስቲያኗንም ስም ያጠፋሉ። ያሳዝናል ዛሬ የተያዘዉ በዚህ መልክ መሰራቱ ነዉ፤ ስለቤተ ክርስቲያን አንድነት ስለወንጌላዊ ትምህርቷ ስለ ጥንታዊ ሥርዓቷ በጠቅላላም ስለ ቤተ ክርስቲያኗ ሕልዉና ባለማሰብ አስመሳይ ካህናት ነን ባይ ቤተ ክርስቲያናችን ነጻ ናት ወይም ገለልተኛ ናት እያሉ አንዱን ከሌላዉ ሲለያዩ የየት ሀገርን ቤተ ክርስቲያን ስም መያዛቸዉ ወይም መጠበቃቸዉ ወይስ የየትኛዋን ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት መከተላቸዉ እንደሆነ እነርሱም እያዉቁትም ለሌላዉ ሊያስረዱ አይችሉም በዚህም ምክንያት የነርሱም ስም ይጠፋል የሕያዊቲቱ ቤተ ክርስቲያን ስም አብሮ ይጠፋል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መልኳን፣ ስሟን፣ አላማዋን፣ አስተዳደሯን መለወጥ ከቶ የለባትም ያችዉ አንዲቷ ቅድስት ሐዋርያዊት ኩላዊት ኢትዮጵያዊት ቤተ ክርስቲያን መሆን አለባት፤ በዚህም ብቻ መታወቅ አለባት። አስተዳደሯ ከላይ ፓትርያርክ ቀጥሎ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ሲሆን መመሪያ ሰጪዉና ሕግ ሠሪዉ፣ ሕግ አስከባሪዉ፣ ሕግ አስፈጻሚዉ ቅዱስ ሲኖዶስ ነዉ። ከዚህ የወጣ በነአቶ በነዶክተር በነሻለቃ በነ. . . . የተቋቋመና የሚሠራ ቤተ ክርስቲያን አይባልም አስተዳደራዊ ሥርዓት ከዚህ ይገኛል ተብሎ አይጠበቅም። በቤተ ክርስቲያን ስም ቤተ ክርስቲያንን ለመምታት ጠላቶችየገዘብ ይሰጣሉ ዲያብሎስ ሰይጣን የሆኑ ሰባኪዎችንም ይልካሉ ሁሉ ከያዙት አላማ ዉጭ እንዲሆኑ ግፊት ያደርጋሉ ለምሳሌ

ሀ - ሲኖዶስ የሚሰጠዉን ቃልና አሰራር ብትተዉት አንድ እንሆን ነበር የሚሉ

ለ - የጳጳሳትን ስም ባታነሱብን እነሱም ባይገዙብን አንድ እንሆን ነበር የሚሉ

ሐ - ሲኖዶሱ ያለዉ አዲስ አበባ ነዉ ያንን ነዉ የምንደግፈዉ ይህንን ተዉና አንድ እንሁን የሚሉ የተለያዩ መሰናክሎችን

ለምዕመናን የሚያስተላልፉ ይገኛሉ።

አንደኛዉ ወገን ሲኖዶሱን አፍርሱና አንድ አንሁን የሚለዉ የቤተ ክርስቲያንን ሕልዉና አጥፋና ሌላ ድርጅት አቋቁመን እንሂድ እንደማለት ነዉ። ቤተ ክርስቲያኗ በቅዱስ ሲኖዶስ ካልተመራች እንደ ከልት መሆኗን ያዉቃሉ ፓትርያርኩም ሲኖዶስ ከሌለ ሥራ የላቸዉም መብትም የላቸዉም ይወድቃሉ ለማለት ነዉ ይህንንም ለምተዉ የሚያስተጋቡ ብዙዎች ናቸዉ።

ሁለተኛዉ ወገን የጳጳሳት ስም ባይነሳ ጳጳሳት ባይኖሩ ቤተ ክርስቲያኖቻችን በአንድነት ይራመዱ ነበር የሚሉት ከምስራቅ እስከ ምዕራብ ከሰሜን እስከ ደቡብ እየተመላለሱ ቡራኬ በመስጠት ትምህርት በማስተማር የሚገኙ አባቶች ከጠፉ ክርስትናዉም ይጠፋል የሚል ዉሳኔ የወሰዱ ይመስላል። እንዲያዉም አንዳንዶች ጳጳሳት ለምን ወጡ ከዚያዉ አይሞቱም ነበር እያሉ ዛሬም በሕይወታቸዉ ለመቅበር ጉድጓድ የሚቆፍሩ አሉ፤ የቤተ ክርስቲያንም ፍለጋዉ ጨርሶ እንዲጠፋ ነዉ።

ሶስተኛዉ ወገን ሲኖዶሱ አዲስ አበባ ነዉ ያለዉ ከአዲስ አበባ አይወጣም የሚሉ የዉስጥ አርበኞች እንዲህ ብሉ ሹመት ሽልማት ታገኛላችሁ እየተባሉ የተወዘዉን የአዲስ አበባንዉን ሲኖዶስ እንዲቀበሉ ለማድረግ ብዙ ጥረት የሚያደርጉ ናቸዉ። ስለዚህ ተግባር በተለያየ መልክና ልብስ ከአዲስ አበባ እየተላኩ ከእኛ ጋር ግንኙነት የሚያደርጉ መስለዉ አላማቸዉን የሚያስፋፉ ብዙዎች ናቸዉ፤ ግን አዉቀንባቸዋል።

የአዲስ አበባዉን ሲኖዶስ እኛ አዉግዘን ሲኖዶስ በአሜሪካ ነዉ ብለናል ምክንያቱም ሕጋዊ ፓትርያርክ አቡነ መርቆሪዎስ የሚመሩት ነዉ፤ ያኛዉ የአዲስ አበባዉ ግን ሕገ ወጥ ነዉ ምክንያቱም በፓትርያርክ ላይ ፓትርያርክ ሁነዉ የተሾሙት ፓትርያርክ አይባሉም በእርሳቸዉ የሚመራ ሲኖዶስ ቅድስና የለውም፤ ስለዚህ ሲኖዶስ አይባልም። የአዲስ አበባዉ ሲኖዶስ ሲቋቋም በመፈንቅል በወታደርም ኃይል ስለሆነ ሲኖዶስ አይባልም።

## ፫ - የቅዱስ ሲኖዶስ ስም መለወጥ ያስፈልጋልን ?

የቤተ ክርስቲያኗን ሕልዉና ለማጥፋት ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንንም ለማፍረስ እንዲቀላቸው ከማድረግ በስተቀር የቅዱስ ሲኖዶስ ስም ሊለወጥ አይቻልም። ያለ ቅዱስ ሲኖዶስ ቤተ ክርስቲያኖች በአንድ መንገድ ሊሄዱም ሊገናኙም አይችሉም። ብዙዎችን የቅዱስ ሲኖዶስ ስም ያስፈራቸዋል ሲኖዶሱ ባይኖር ቤተ ክርስቲያኖች አንድ ይሆኑ ይገናኙ ነበር በማለት ሳያፍሩ ሳይፈሩ የሚናገሩ አሉ። ቅዱስ ሲኖዶስ የሚያስቸግረዉ ስሙ ነዉን ወይስ ግብሩ ? ቅዱስ ሲኖዶስ ቃሉ የውጭ (የግሪክኛ) ቢሆንም የቤተ ክርስቲያናችን ቃል ሆኖ ለብዙ ምዕት ዓመታት ሲሰራበት ቆይቷል ተግባሩም የቤተ ክርስቲያንን አንድነት ለመጠበቅ ሥርዓቱም እንደጸና ለመጠበቅ በቤተ ክርስቲያን ሰላምን ለመፍጠር የቅዱስ ሲኖዶስ ተቋም በጣም አስፈላጊ ነዉ።

እንግዲህ የሚለወጠዉ የትኛዉ ነዉ ስሙ ወይስ ግብሩ? ስሙም ግብሩም የሚለወጥበት ምክንያት የለም ሊኖርም አይችልም፤ ስሙንም ግብሩንም ለቆ ወይም አጥፍቶ ሥርዓት አልበኝነት ከመሆን በቀር። በመጀመሪያ ሲኖዶስ የሚለዉ ስም እንዲለወጥ ከሚያስኘበት ምክንያቶች አንደኛዉ ምን ይሆን? ጉድለት ተገኘበት? ወይስ ሸክሙ ከባድ ሆነን? ወይስ ከአዲስ አበባዉ ሲኖዶስ ጋር አይተባበርም በማለት ነዉን? ወይስ በዚያ ስም ተጠራ እንደማለት ነዉን?

ይህንን ሁሉ ያተትነዉ ከምዕመናን ዉስጥ እንደ ሸማግሌዎች እየሆኑ ቤተ ክርስቲያኖች አንድ እንዲሆኑ፤ ቤተ ክርስቲያኖች በአንድ ሕግ ሥር እንዲተዳደሩ እንቅፋት የሆነን ሲኖዶስ የሚለዉ ስም ነዉ እርሱ ቢለወጥ ሁላችን በአንድ ላይ እንሠራ አንድም ሆነን እንራመድ ነበር የሚል ምክንያት ስለሚያቀርቡ ነዉ። ይህ ሰባራ ምክንያት ቤተ ክርስቲያንን የሚለያይ እንጂ አንድ የሚያደርግ ማሰሪያ የሌለዉ ነዉ። ብዙዎች ቤተ ክርስቲያኖች በአንድ ላይ እንዲሄዱ ያደረጋቸዉ ቅዱስ ሲኖዶስ ነዉ፤ በውጭ ያሉ ወደዚህ ቅዱስ ሲኖዶስ ይግቡ አንድም ይሁኑ በማለት ፋንታ ለመለያየት የሚሰጥ ምክንያት ሆኖ አግኝተነዋል።

ቅዱስ ሲኖዶስ ቀርቶ ቤተ ክርስቲያንን አንድ የሚያደርግ ሁሉን የሚያስተሳስብ አመራር የሚሰጥ ሌላ ምን ቃል

ይተካበታል? እርሱስ የሚወገድበት ምን ጉድለት ስላስከተለ ነዉ? ወይስ ምን እንቅፋት ስለፈጠረ ነዉ? በቅዱስ ሲኖዶስ የታቀፉትን ቤተ ክርስቲያኖች ለመበተን፤ እንደ ሌሎች ሥርዓት አልባ ለማድረግ ካልሆነ በቀር።

ስብሰባ፣ ማሕበር፣ ጉባኤ፣ ምክር ቤት ሌላም ይህን የመሳሰሉ ቃላት ቢደረደሩ የሲኖዶሱን ትርጉምና ስሜት ሊሰጡ አይችሉም፤ ስለዚህ የብዙኃን ሊቃነ ጳጳሳት ስብሰባ ወይም ጉባኤ ስሙ ቅዱስ ሲኖዶስ ነዉ። አሁንም የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት በዚህ ቅዱስ ሲኖዶስ መታቀፍ አለባቸዉ የራቁት መቅረብ አለባቸዉ አንድነታቸዉን መለግጽ በአንድ ሲኖዶስ ስር እንዲመሩ መደረግ አለባቸዉ።

ቅዱስ ሲኖዶስ ለአንድነት አመች ነዉ እንጂ እንቅፋት አይደለም፤ ቅዱስ ሲኖዶስ ለሁሉ ቀጥተኛ መመሪያ ይሰጣል፤ ሁሉንም በስነ ሥርዓት ይመራል እንጂ አፍራሽ አይደለም። ከቅዱስ ሲኖዶስ ዉጭ መሆን ግን በሕገ ወጥነት ለመኖር ለመሰራት ነዉ። ሲኖዶስ ይቅር ማለት ለስሁተት አመች እንዲሆን ነዉ።

ቤተ ክርስቲያን እስከአለች ቅዱስ ሲኖዶስ ይኖራል ቅዱስ ሲኖዶስም እስካለ ቤተ ክርስቲያን ትኖራለች።

ሁላችን በቅዱስ ሲኖዶስ አስተባባሪነት አንድነት እንራመድ የቤተ ክርስቲያንን የአንድነት አርማ እናንሳ! ስለ ቤተ ክርስቲያን እናስብ፤ እንናገር፤ እንስራ። ሲኖዶሱም ዓላማዉ ይኸ ስለሆነ ጥሪዉን ለሁሉ ያስተላልፋል!

አባ መልከ ጼዴቅ ሊቀ ጳጳስ
የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ፀሐፊ